# *የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ተጠናክሮ ይቀጥላል*

የታላቁን ሕዳሴ ግድብ በሚመለከት የግብጽ አንዳንድ ባለሥልጣናት፣ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችና የሲቪል ሶሳይቲ ኃላፊዎች ሲያካሄዱ የከረሙትን አፍራሽ ፕሮፓጋንዳ በሚመለከት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ግንቦት 28 ቀን 2005 ዓ.ም ያወጣው መግለጫ ይታወሳል፡፡

በዚህ መግለጫ ኢትዮጵያ በጉዳዩ ላይ ያላትን ገንቢ አቋም ገልጻ ነገር ግን በግብጽ በኩል የግብጽን አቋም በኢትዮጵያ የግብጽ አምባሳደርን ከአንዴም ሁለቴ ጠርታ መጠየቋና ለግብጽ መንግስት ጥያቄ ማቅረቧ ይታወቃል፡፡ ኢትዮጵያ ከምንም በላይ ለትብብር፣ ለወዳጅነትና ለጋራ ጥቅም ያላትንም ጽኑ እምነት በወቅቱ ግልጽ አድርጋለች፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ በትላንትናው ዕለት ማለትም ሰኔ 3 ቀን 2005 ዓ.ም ብሔራዊ የናይል ኮንፍራንስ (International conference of the Nile) በተሰኘው ስብሰባ ፕሬዝዳንቱ፣ ጠ/ሚኒስትሩ፣ ሚኒስትሮች እና ሌሎችም በተገኙበት ታላቁን የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ አስመልክቶ አፍራሽ መልዕክቶች ሲተላለፉ ቆይተዋል፡፡

ከነዚህም መካከል የህዳሴ ግድብ በግብጽ ላይ አደጋ በመደቀኑ፣ በኢትዮጵያ ላይ በተለያዩ መንገዶች ተጽዕኖ የማሳረፍና የግድቡን ግንባታ እንድታቆም የማድረግ እንቅስቃሴ ስለማድረግ፣ በአጠቃላይ ከኢትዮጵያ ፍላጎትና አድራጎት ውጭ እንዲሁም የህዳሴ ግድቡን እንዲያጠና ግብጽ ጭምር ያለችበት ዓለምአቀፍ የኤክስፐርቶች ቡድን ያቀረበውን ዘገባ ጭምር የሚያጣጥሉ ጠብ አጫሪ አስተያየቶች በመድረኩ ሲስተናገዱ ተስተውለዋል፡፡

በዚህ ረገድ በግብጽም ሆነ  በሌላ ማንኛውም ወገን የሚቀርብ የግድቡን ግንባታ የማዘግየት ወይንም ከነአካቴው የማቋረጥ ነገር ፈጽሞ ተቀባይነት የለውም፡፡ በህዳሴው

ግድብ ሸፋን የውስጥ ችግርን ለማቃለል የሚደረገው ጥረት የግብጽን ዘላቂ ጥቅም አይጠብቅም፡፡

ጦርነትና ሌሎች አፍራሽ ስልቶችን ስለመጠቀም የሚቀርቡት ሃሳቦች ያረጁና ያፈጁ የ21ኛውን ክፍለ ዘመን አስተሳሰብ የማይሸከሙ ጤናማ ያልሆነ አስተሳሰቦች ሲሆኑ ኢትዮጵያ በዚህ ቀረርቶ ተደናግጣ ግንባታውን ለሰኮንድም እንደማታቆም ታረጋግጣለች፡፡ የግብጽ ወገንም ከዚህ አፍራሽ ድርጊት ተቆጥቦ ለሁለቱ አገሮች ግንኙነት መጠናከር የበኩሉን ጥረት እንዲያደርግ እናሳስባለን፡፡

በዚህ አጋጣሚ የሱዳን ማስታወቂያ ሚኒስትር የህዳሴ ግድቡን ጠቀሜታ አስመልክተው ያሰሙት ሃሳብ ገንቢ በመሆኑ ሊመሰገኑ ይገባል፡፡ ሌሎችም ከዚህ የሚቀስሙት ትምህርት እንዳለ እንገምታለን፡፡

በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ይህ ግድብ ግብጽን ጭምር የሚጠቅም መሆኑን እንደገና እያሳሰበች ከግብጽ ጋር በወዳጅነትና በትብብር ለመሥራት ጽኑ ፍላጎት እንዳላት ትገልፃለች፡፡

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

የቃል አቀባይ ጽ/ቤት

ሰኔ 04 ቀን 2005 ዓ.ም